# የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ)

Ethiopian People's Congress for United Struggle (Shengo)

www.ethioshengo.org    shengo.derbiaber@gmail.com

## የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ ሁለተኛ ጉባዔውን በተሳካ ሁኔታ አጠናቀቀ

ሰኔ ፳፱ ቀን ፪ ሺህ ፭ ዓ. ም
July 6, 2013

የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ ከሰኔ ፳፮ ቀን እስከ ሰኔ ፳፰ ቀን ፪ ሺህ ፭ ዓ. ም ድረስ (July 3-5, 2013) በሲልቨር ስፕሪንግ ሜሪላንድ (Silver Spring, MD) ያካሄደውን ሁለተኛ ጉባዔውን በተሳካ ሁኔታ አጠናቀቀ። ጉባዔው የተከፈተው ሰኔ ፳፮ ቀን ፪ ሺህ ፭ ዓ. ም ከጠዋቱ አራት ሰዓት ላይ (10:00 am) ሲሆን በጉባዔው መክፈቻ የ13ቱ የሸንጎ አባል ድርጅቶች ተወካዮች፤ የሃይማኖት መሪዎች፤ የተለያዩ ድርጅቶች ወኪሎችና ጥሪ የተደረገላቸው ደጋፊዎችና ታዋቂ ግለሰቦች በመክፈቻው ሥነ ሥርዓት ላይ ተገኝተዋል።

ሁለተኛው የሸንጎ ጉባዔ የተጀመረው የመጀመሪያውን ቀን ለሕዝብ ክፍት በማድረግ ነበር። በጉባዔው አዘጋጅ ኮሚቴ ሊቀመንበር በፕሮፌሰር አቻምየለህ ደበላ የ"እንኳን ደህና መጣችሁ" ንግግር ነበር ጉባዔው የተከፈተው። ከዚያም በስደት ላይ የምትገኘው የሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርሰቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የሀገረስብከቱ ሊቀ-ጳጳስ አቡነ ሣሙኤል ፀሎተ-ቡራኬ በማድረግ ጉባዔው የተሳካ እንዲሆን ምክራቸውን ለግሰዋል። እንዲሁም የኢትዮጵያውያን የእስልምና ሃይማኖት የመጀመሪያው ሂጅራ ተከታዮችን በመወከል አቶ ነጂብ ሁለተኛው ጉባዔ የተሳካ እንዲሆን ያላቸውን ምኞት በመግለጽ የተቃዋሚ ኃይሎች ተባብረው እንዲታገሉ አሳስበዋል። ከዚያም ከሜልቦርን፤ አውስትራሊያ ከሸንጎው ደጋፊ አካል የተላከው የድጋፍ መልዕክት ተነቦ ሌሎችም ድርጅቶች የድጋፍ መልዕክቶቻቸው እንዲቀርቡ ተደረገ።

በመቀጠልም የሸንጎው ሊቀመንበር ዶ/ር ኤርምያስ ዓለሙ ሸንጎው ባለፈው አንድ ዓመት ያከናወናቸውን ዋና ዋና ተግባራት ለተሰብሳቢው አቅርበዋል። ከዚያም በተለያዩ ወቅታዊና ርዕሶች ላይ ጥናታዊ ጽሁፎች ቀርበዋል። በመጀመሪያ "ኢትዮጵያ ከየት ወዴት" በሚል ርዕስ የሀገራችንን የወቅቱን ሁኔታ በፖለቲካው፤ በኤኮኖሚውና በማኅበራዊ ገጽታዎች ላይ ያተኮረው ፅሁፍ በዶ/ር አክሎግ ቢራራ፤ "የኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት በህወሓት/ኢህአዴግ የደረሰበት ጥቃት፤ ሊደርሱ የሚችሉ አደጋዎችና ያሉን አማራጮች" በሚል ርዕስ በአቶ መርሻ ዮሴፍ፤ "ሸንጎው ይዞት የተነሳው አብይ የጋራ ትግል ስትራቴጂና አቅጣጫ" በፕሮፌሰር አቻምየለህ ደበላ፤ "የብሄራዊ መግባባትና የሰላምና ዕርቅ አማራጭ ጥያቄ" በአቶ ሀገሬ አዲስ ቀርበው ሰፊ ውይይቶች ተካሂደዋል። በተጨማሪም "አሃዳዊና ፌደራላዊ ሥርዓተ-መንግሥታት በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ በዶ/ር አረጋዊ በርሄ

Tel: 44 7937600756 , +1 9168486790 E-mail : shengo.derbiaber@gmail.com

የተዘጋጀውን ጥናታዊ ፅሁፍ አዘጋጁ በአካል ማቅረብ ባይችሉም ፅሁፉ ለተሰብሳቢዎቹ እንዲሰራጭ ተደርጓል። ውይይቶቹ ሀገራችንና ሕዝቧ የሚገኙበትን ሁኔታ በስፋት የቃኙ ነበሩ። ሸንጎው የጀመረውን ለፍትሃዊ ሥርዓት ለውጥ ማምጣት የተጠናከረ የትግል ማዕከል ምሥረታ ትክክለኛና ዓይነተኛም አማራጭ መሆኑን በተደጋጋሚ ተገልጾ የስብሰባው ተሳታፊዎች የተለያዩ ገንቢ አስተያየቶችና ምክሮችን በመለገስ የዕለቱ ሕዝባዊ ስብሰባ ተጠናቀቀ።

የመጀመሪያው ቀን ስብሰባ ከተጠናቀቀ በኋላ በቀጣዮቹ ሁለት ቀናት ደግሞ የጉባዔው ልዑካን በተዘጋጀው አጀንዳ መሠረት ሰፊና ጥልቅ ውይይት አካሂደዋል። ጉባዔው በሀገሪቱ የተለያዩ ሁኔታዎች፤ በሥራ አፈጻጸሙ፤ በትግል አቅጣጫውና በአቅም ግንባታ ጉዳይ ላይ ሰፊ ውይይት አካሂዶ ራዕዩን አጥርቶ አሠራሩንና አመራሩን አጠናክሮ መውጣት እንደሚገባው አረጋግጠ ተግባራዊ አድርጓል። ሸንጎው ለኢትዮጵያ ሕዝብ የገባውን ቃል እውን ለማድረግ የሚያስችል ተጨባጭ ስትራቴጂያዊ ውሳኔዎችን ከመወሰኑም ባሻገር ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችለውን የመዋቅርና አሠራር ማስተካከል አድርጎ ለመጪው ሁለት ዓመታት የሚያገለግሉ የአመራር አባላትን መርጧል።

ጉባዔው አገራችን አሁን ከምትገኝበት የአምባገነን አገዛዝ ተላቅቃ የዜጎች መብቶች የሚከበሩባት፤ ፍትኅና የሕግ የበላይነት የሰፈነባትን ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመመሥረት፦

1. የተቃዋሚ ኃይሎች ኃይላቸውን አስተባብረው መታገልን ሁኔታው የግድ የሚለው መሆኑን በመገንዘብና ተባብረው መሥራት እንደሚገባቸው በማመን የሸንጎውን የትብብር ጅማሮ እንዲቀላቀሉ ለተቃዋሚ ኃይሎች ሁሉ የትብብር ጥሪውን ያቀርባል።
2. ሸንጎው በሀገር ውስጥ የሚገኙ ድርጅቶች የሚያደርጉትን ትግል ይደግፋል፤ በማንኛውም መልኩ ለመተባበር ዝግጁነቱን ያረጋግጣል።
3. በሀገራችን ላይ የተጫነው አምባገነናዊ አገዛዝ ያከትም ዘንድ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድነት እንዲነሳና ትግሉን በቀጣይነትና በጽናት እንዲቀጥል ሸንጎው እያሳሰበ አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁነቱን ያረጋግጣል።
4. የመከላከያና የፖሊስ ኃይሎች የአምባገነኑ አገዛዝ የመጨቆኛና የማፈኛ መሣሪያ ሳይሆኑ የሀገርንና የወገንን ደህንነት ለማስጠበቅ የተቋቋሙ ኃይሎች መሆናቸውን በመገንዘብ ከሕዝብ ጎራ እንዲወግኑ ሸንጎው ጥሪውን ያቀርባል።
5. ሸንጎው በኃይማኖት ተቋማት ውስጥ የሚደረገውን ጣልቃገብነት እያወገዘ ምዕመናኑ ጠንክረው በመቆም በጋራ መታገል እንደሚገባቸው ያምናል፤ ያሳስባልም።
6. የፖለቲካ እስረኞች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱና የፕሬስ ማለትምና ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት እንዲከበር ሸንጎው ይታገላል።
7. ዜጎች ኢ-ሰብዓዊ በሆነ መልክ ከቀዬአቸው መፈናቀላቸውን ጉባዔው አውግዞ ማንኛውም ዜጋ በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል የመኖርና ተዘዋውሮ የመሥራት መብቱ እንዲከበር ይታገላል።

8. የሀገራችን ለም መሬት ለባዕዳን መቸርቸሩ በአስቸኳይ መቆም እንዳለበት በማመን ድርጊቱ እንዲቆም ጠንክሮ ይታገላል።
9. ወገኖቻችን በተለይም ሴቶች እህቶቻችን ወደ ዐረብ አገር መሰደድና መሰቃየት ተጠያቂው አምባገነኑ አገዛዝ መሆኑን ጉባዔው አስምሮበት ይህ ስደት በአስቸኳይ መቆም ይኖርበታል ይላል፤ ለዚህም ይታገላል።
10. ባለሥልጣናት በሙስና መዘፈቃቸውን በመገንዘብ ሙስናን ለማጥፋት አስፈላጊው እርምጃ መወሰድ እንዳለበት ጉባዔው አምኖ ያለአግባብ የሀገራችንን ድንበር አቋርጦ የወጣው የሀገር ሀብት ወደሀገር እንዲመለስ ይታገላል።
11. ሸንጎ በሀገራችን ሉዓላዊነት ላይ የሚቃጣውን ማንኛውንም ሙከራ አጥብቆ እንደሚያወግዝና ሕዝባችን የሀገሩን ዳር ድንበር ነቅቶ እንዲጠብቅ በማሳሰብ ሸንጎውም የድርሻውን ለማበርከት ዝግጁ መሆኑን ያረጋግጣል።

በመጨረሻም በወገኖቻችን ግፍና ሰቆቃ፤ በአገራችንም ላይ ብሄራዊ ውርደትና ከፍተኛ የጎልውና ጥያቄ ከፊቷ ተደቅነዋል። ከዚህ ከፍተኛ አደጋና ቀውስ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመውጣትና ወገኖቻችን የሰላምና የዴሞክራሲ አየር እንዲተነፍሱ ለማድረግ በጋራ ለመታገል የሚያስችለውን የሸንጎውን የትብብር አማራጭ የአገራቸው ጉዳይ የሚያሳስባቸውና የሚያንገበግባቸው አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ድጋፋቸውን እንዲሰጡት ሸንጎው በአክብሮት ይጠይቃል።

ኢትዮጵያ በተባበሩት እውነተኛ ልጆቿ ትታደጋለች!
ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!

Tel: 44 7937600756 , +1 9168486790 E-mail : **shengo.derbiaber@gmail.com**